Kirklees COUNCIL

wakefieldcouncil working for you

# የእከክ በሽታ



## የኢንፌክሽን መከላከያ እና ቁጥጥር መረጃ ቡክሌት

# የእከክ በሽታ

የእከክ በሽታ የተለመደ እና ማንንም ሰው ሊይዝ የሚችል ነው።. መስፋፋቱን ለስማቆም በፍጥነት መታከም አለበት።

የእከክ በሽታ መሆኑን ያረጋግጡ

ምልክቶቹ የሚከተሉት ናቸው:

- ከባድ የማሳከክ ስሜት፤ በተለይም በማታ
- ከፍ ያለ ሽፍታ ወይም ነጠብጣቦች

ነጠብጣቦቹ ቀይ ሊመስሉ ይችላሉ. በጠይም/ጥቁር የቆዳ ቀለም ላይ ለማየት በጣም አስቸጋሪ ቢሆኑም ስሜቱ ይሰማዎታል።.



ጥቃቅን ቅንቅኖች በቆዳ ውስጥ እንቁላል ይጥላሉ፤ በዚህም በአንደኛው ጫፍ ላይ ነጥብ  ያላቸውን መስመሮች ያስቀምጣሉ።



ሽፍታው የትም ቦታ ሊከሰት ይችላል፤ ነገር ግን በአብዛኛው የሚጀምረው በጣቶች መካከል ነው።



ሽፍታው ጠቆር ያሉ ነጥብጣቦችን ቆዳ ላይ ሊተው ይችላል። ይህም ጠይም/ጥቁር ቆዳ ላይ ቡናማ ወይም ጥቁር ሆኖ ይታያል፡ ፡



ከዚያም በኋላ ሽፍታው ተሰራጭቶ ወደ ጥቃቅን ነጠብጣቦች ይቀየራል። ይህም ቀላ ባለ ቆዳ ላይ ቀይ ሆኖ ይታያል።

# የእከክ በሽታ

የእከክ በሽታ ብዙውን ጊዜ ከባድ ባይሆንም ነገር ግን መታከም ያስፈልገዋል፡፡ እንደ ችፌ ያሉ አንዳንድ ሁኔታዎችን ሊያባብስ ይችላል፡፡

የእከክ በሽታ በጣም ተላላፊ ቢሆንም ሽፍታው እስኪታይ እና እስኪታወቅ ድረስ እስከ 8 ሳምንታት ሊወስድ ይችላል።

ሽፍታውን ማከክ የቆዳ ኢንፌክሽን ሊያስከትል ይችላል፡፡

የበሽታው ምልክቶች የሌላቸውን እንኳን ጨምሮ ሁሉም ሰው በተመሳሳይ ጊዜ መታከም አለበት፡፡

# ስርጭት

## በበሽታው ከተጠቃ ሰው:

በእከክ በሽታ ከተያዘ ሰው ጋር በቀጥታ ቆዳ ወደ ቆዳ ንክኪ።

10 ደቂቃ ገደማ የማይቋረጥ የቆዳ-ለቆዳ ንክኪ።

ቅንቅኑ ከሰው ወደ ሰው መዝለል አይችልም ነገር ግን ለአጭር ጊዜ የቆዳ ለ ቆዳ ንክኪ ሲኖር ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ሊዛወር ይችላል፤ ለምሳሌ እጅ ለእጅ በመያያዝ፣ በግብረ ሥጋ ግንኙነት።

# ለእከክ በሽታ የሕክምና እቅድ

## የማጥፋት ቀን 1

ከህክምናው በፊት ገላዎን አይታጠቡ።  ሎሽን / ክሬም በቀዝቃዛ ቆዳ ላይ መደረግ አለበት።

የእጅ መዳፍ፣ የውስጥ እግር ፣ የተቆረጡ እና ንፁህ የጣት እና እግር ጥፍሮች ስር፣ አንገት፣ ፊት፣ ጆሮ እና የጸጉር መሳሳት ካለ ደግሞ የራስ ቅልን ጨምሮ የሁሉንም የሰውነት ክፍሎች መዳረሳቸውን ያረጋግጡ።

አምራቹ ከተወሰኑ ቡድኖች በስተቀር ከአንገት በላይ ያለውን ቦታ ማዳረስ ምክር ላይሰጥ ይችላል ነገርግን የባለሙያዎች አስተያየት እንደሚያሳየው ይህ ቦታ በሁሉም ጉዳዮች / ግንኙነቶች መታከም አለበት። መላውን ሰውነት ለመሸፈን ከአንድ በላይ የሎሽን/ክሬም እቃ ሊያስፈልግ ይችላል።

ምርቱ ከተወገደ (ለምሳሌ እጅን በሚታጠብበት ጊዜ ወይም በመጸዳጃ ጊዜ) እንደገና መደረግ አለበት።

ክሬሙ / ሎሽን በአምራቹ እንደታዘዘው ህክምናን ተከትሎ መወገድ አለበት።

በቀን ውስጥ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ህክምና ስለማይወገድ በአንድ ሌሊት (ቢያንስ ለስምንት ሰአታት) ማድረግ በጣም ውጤታማ ነው።

ክሬሙ / ሎሽኑ በአምራቹ እንደታዘዘው ህክምናን ተከትሎ መወገድ አለበት። ከህክምናው በኋላ አልጋዎችን እና ልብሶችን ይጠቡ።

ሁሉም ሠራተኞች በተመሳሳይ 24 ሰአት ውስጥ ህክምና ማድረግ አለባቸው።

## የማጥፋት ቀን 2

የመጥፋት ቀን 1 ካለፈ ከ 7 ቀናት በኋላ ሁሉንም እርምጃዎች ይድገሙ።

**ሁሉም በተመሳሳይ 24 ሰዓታት ውስጥ።**

## ያግኙን

የኪርክሊስ እና ዌክፊልድ የኢንፌክሽን መከላከል እና ቁጥጥር ቡድን (Kirklees & Wakefield Infection Prevention and Control Team)

ኢ-ሜይል:

infection.control@kirklees.gov.uk

ስልክ: 01484 221000

ዌብሳይት:

www.kirklees.gov.uk/infectioncontrol

የዩናይትድ ኪንግደም የጤና ደኅንነት ኤጀንሲ (UKHSA)

ስልክ: 0113 386 0300

ከሥራ ሰዓት ውጪ ምክር 0151 909 1219